# የጠብ ጫሪው አካሄድና የኢትዮጵያ እርምጃ

ይነበብ  ይግለጡ 06-30-17

የኤርትራው መንግስት በሁሉም ጎረቤቶቹ ዘንድ በጠብ ጫሪነት ፖሊሲው ይታወቃል፡፡ በዚህም መሰረት ከየመን  በሀኒሽ ደሴቶች፤ ከኢትዮጵያ  በባድመ መሬት፤ ከጅቡቲ ጋር ደግሞ በዱሜራ ደሴቶች ውዝግብና ጦርነት ውስጥ እስከ መግባት ደርሶአል፡፡ በሁሉም አቅጣጫ የሄደበት መንገድ አላዋጣው ያለው የኤርትራ መንግስት ከሁሉም የከፋ ውድቀት ያስከተለበት በራሱ ትንኮሳ ከኢትዮጵያ ጋር የለኮሰው የባድመው ጦርነት ነው፡፡

የኤርትራው መንግስት ራስ ሳይጠና ጉተና እንዲሉ ሆኖ ገና ከጫካ ጦርነት ማግስት ወደ መንግስትነት የተለወጠው ከአረብ ጀነራሎች ጋር ከውጊያው በፊት ዶልቶ የተነደፈ የጦር ዘመቻና እቅድ ይዞ ምሽጎቹን በተራራ ድንጋዮች ላይ ገምብቶ ብዙ አመታት እዋጋበታለሁ ብሎ ይሄንኑም በአረብ ጀነራሎች አስጎብኝቶ የመሣሪያና የአማካሪ ድጋፍም ተደርጎለት አጸድቆ ሲያበቃ ጦርነት ከፈተ፡፡

በአረብ ጀነራሎች በተሰጠው ሙያዊ አስተያየት *ማንም ይህንን ምሽግ ተራምዶ ድል ሊያደርግህም* ተብሎ፣ ተወድሶና ተመርቆ አክላልቶ ጦር የሰበቀው ሻእቢያ ኢትዮጵያ አሁን አቅም የላትም፤ መደበኛ ሠራዊትዋ ፈርሶአል፤ ኢሕአዴግ ገና አዲስ መንግስት ስለሆነ ሊቋቋመን አይችልም በሚል እብሪት ተሞልቶ፣ ታንክና መድፍ አሰልፎ ነበር የባድመ ወረራን ያካሄደው፡፡  ያሉትን ጥቂት አውሮፕላኖች አስነስቶ በመቀሌ አይደር ሕጻናት ትምህርት ቤት ላይ አረመኔያዊ የቦምብ ጭፍጨፋ ያደረገው፡፡

ለዚህ እብሪትና ድንፋታ ከአቅም በላይ መንጠራራቱ በእልህ በብስጭትና በቁጣ በከፍተኛ ብሔራዊ ስሜት ገንፍሎ በአራቱም የኢትዮጵያ ማእዘናት በመውጣት አዝምቱን እንዋጋለን በሚል እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ የተነሳውን ወትሮም አትንኩኝ ባዩንና ከተነካም የማይመለሰውን ሕዝብ መንግስት ለማዝመት ከሚችለው በላይ ሁኖ የተቀበለውን ተቀብሎ ዘመቻው ቀጠለ፡፡

በእግረኛ በታንከኛ በአየር በመድፍ በመካናይዝድ በተደረገው እልህ አስጨራሽና በአይነቱ በአፍሪካ ገጠመኝ የሌለው በተባለለት ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት በታላቅ ጀግንነትና

መስዋእትነት በኢሳያስ አፈወርቂና በአረብ የጦር ጀነራሎች ጣምራነት ኢትዮጵያን ከተለያየ አቅጣጫ ለማጥቃት በብዙ ጥናት የተነደፈውን የማጥቃት እቅድ በተጠናከረና በተደራጀ መከላከል አስተማማኝ ድል መጨበጥ እንችላለን ሲሉ ያዘጋጁትን በድንጋይ ተራራዎች ላይ የተገነባ ምሽግ በአስደናቂ ተጋድሎና ጀግንነት በመናድና በመደርመስ በቁጥጠር ስር አዋለው፡፡

የሻእቢያ የቆረጣ ስልት በዳግም ቆረጣ በመከፋፈል ባልተጠበቀና ድንገተኛ ማጥቃት በከበባና በታትኖ በመምታት ስልቶች ተመቱ፡፡ የሻእቢያ ማዘዣ ጣቢያዎች የሬድዮ የአየር መገናኛ የስንቅ ትጥቅ ማከመቻ ዴፖዎች የራዳር ጣቢያዎች የሠራዊቱ የመገናኛ መስመሮች፣ የቀለብና ትጥቅ ማስተላለፊያ ድልድዮች፣ የግንኙነት አውታሮቹ ግዜያዊና ቋሚ የአየር ማረፊያዎቹ በንስሮቹ የኢትዮጵያ ጦር ጀቶች እንዳልነበሩ ሆነው ፈራረሱ፡፡

ተዋጊ ሔሊኮፕተሮቻችን የሻእቢያ ሠራዊት የመሽገባቸውን ምሽጎች እያመሳቀሉ በመደብደብ ተዋጊው ሠራዊት ከምሽጉ ወጥቶ እጁን እንዲሰጥ አስገደዱት፡፡ "አምበሳው አሸው" የሚለውና ሕዝባዊ ተጋድሎን የሚያወድሰው ዘፈን የተዘፈነው የዛን ግዜ ነው፡፡ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በጦርነቱ ግምባር ቢወድቁም ሀገራቸውንና ድንበራቸውን አስከብረው አልፈዋል፡፡ ክብር ለወደቁት ስማእታት ወንድሞቻችን ይሁን፡፡

የሻእቢያ ሠራዊት በብዛት የተማረከበት በራሱ በውስጡ ከፍተኛ የፖለቲካ ቀውስ የተፈጠረበት፣ የተወሰነ የኢኮኖሚ አቅሙ ተሟጦ ያበቃበት ታላቅ ቀውስ ውስጥ የገባበት ሁኔታ ነበር የተፈጠረው፡፡ ከዛን ግዜ ወዲህ የመንግስታቱ ድርጅት ሰላም አስከባሪ ኃይል (አንሚ) በሁለቱ ሀገራት የጋራ መሬት ላይ ሰፍሮ ለቆ እስከወጣበት ግዜ ድረስ ሰላምም ጦርነትም የሌለበት ቀጣና ሁኖ እስከዛሬም ዘልቆአል፡፡

ቀጠናው ጦርነትም ሰላምም የሌለው ነው ሲባል ሻእቢያ በአካባቢው በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች ላይ በተለያየ ግዜ ትንኮሳ እየፈጸመ አፈና እያካሄደ ተኩስ የመክፈት ሁኔታዎችን ይፈጽም ስለነበር አልፎ አልፎ ወታደራዊ ግጭቶች ይከሰቱ ነበር፡፡ ለዚህ የሻእቢያ ትንኮሳ ኢትዮጵያ ተመጣጣኝ የአጸፋ ምላሽ ስትሰጥ ቆይታለች፡፡ በአለፈው አመት አካባቢ ከበድ ያለ ግጭት በሁለቱ ሀገራት መካከል ተካሂዶአል፡፡

ሻእቢያ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያደርገው የፊት ለፊት ግጭትና ጦርነት የትም እንደማያደርሰው ከተረዳ ውሎ አድሮአል፡፡ ከዛን ግዜ ጀምሮ እያካሄደ ያለው የውክልና ጦርነት (ፕሮክሲ ዋር) ነው ፡፡

ይህ የቀየሰው አዲስ ስልት ተላላኪ ጸረ ኢትዮጵያ ኃይሎችን በማዘጋጀት በመመልመል በማሰልጠንና አስታጥቆ በማሰማራት በሶማሊያ አልሻባብን፤ ከሀገር ውስጥ ተቃዋሚ ነን ከሚሉት ደግሞ ኦብነግን፣ ኦነግን፣ ግንቦት ሰባትንና አርበኞችን የተለያየ ስም በመስጠት ብዙዎችን በማደራጀት በአፋር፣ በሶማሊያ፣ በጋምቤላ፤ በደቡብ ሱዳን በሱዳን አቅጣጫዎች ዙሪያ ገባውን ሀገራችንን ቀስፎ ለመያዝ ከትላንት እስከዛሬ ያላባራ ትግል እያደረገ ይገኛል፡፡

ሻእቢያ በተደጋጋሚ ያደረጋቸው ሙከራዎች ከሽፈዋል፤ መክነዋል፡፡ አልፎ ተርፎም አዲስ አበባ ውስጥ በሰላማዊው ነዋሪ ሕዝብ ላይ የአጥፍቶ ጠፊዎች አደጋ እንዲደርስ በሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት፤ ሕዝብ በብዛት በሚገኝባቸው ቦታዎች ላይ የፈንጂና የቦምብ አደጋ እንዲጣል የወሰነው ሻእቢያ ድርጊቱን ፈጻሚ ጀሌዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ ሳይሰማሩ በፊት በኢትዮጵያ የደሕንነት ክትትል ስር እየወደቁ እጅ ከፍንጅ የተያዙበት ምስጢራቸውን ይፋ ለማድረግ የተገደዱበትን ሁኔታ በተደጋጋሚ አይተናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሻእቢያ ዛሬም ወደፊትም አይተኛም፡፡

ዛሬ አንገቱን ቀና ያደረገው ከአረቡ የገልፍ ሀገራት ጋር በተያያዘ የተሰጠው የአይዞህ ባይነትና ሰፊ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን በዚህም መሰረት የአሰብን ወደብ የገልፉ ሀገራት በየመን ላይ ለሚያደርጉት ወታደራዊ ዘመቻ ወታደራዊ ጦር ሰፈር አድርጎ እንደልብ እንዲጠቀሙበት ሰጥቶአቸዋል፡፡

ሁኔታው እንደታወቀ አምና አከባቢ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ሳኡዲ አረቢያ ድረስ በመሄድ ስለጉዳዩ አሳሳቢነት ተነጋግረው ኢትዮጵያ ራስዋን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ለመከላከል ዝግጁ የመሆንዋን አቋም አስታውቀው ተመልሰዋል፡፡ ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ በራስዋ አቅጣጫ ያለውንና ሊኖር የሚችለውን ማንኛውንም ታሳቢና ምናልባታዊ ግምታዊ ሁኔታ ነቅታ የምትከታተል መሆኑ ይታወቃል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ወሳኝ ግዙፍና ዘመናዊ የደሕንነትና የመከላከያ ሠራዊት ያላት ሀገር ነች፡፡ አሁን ከሰሞኑ ችግር መፍጠር የማይታክተው ሻእቢያ ኳታርና ወታደሮች በጅቡቲና በኤርትራ አወዛጋቢ ይዞታ የነበረውን የራስ ዱሜራ ተራራና ደሴቶች በሰላም አስከባሪነት ሰፍረውበት ኖረው ኳታርና ከገልፉ ሀገራት መገለልዋን ምክንያት በማድረግ በድንገት ለቀው ሲወጡ ሻእቢያ ተንደርድሮ ገብቶ ተራራውንና  ደሴቶቹን ይዞአል፡፡

ችግሩ በአዲስ መልክ ማገርሸቱ ብቻ ሳይሆን ወደእኛ የሚያቃርበው አመላካች የሆኑ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ኤርትራ፣ ሳኡዲ አረቢያ፣ ኳታርና ኩዌት የገልፉ ሀገራት የመከላከያ እዝና ሠራዊታቸውን፣ የጦር ጀቶቻቸውንና ተዋጊ መርከቦቻቸውን አሰብ ላይ አድርገው በየመን ላይ ዘመቻ እያደረጉ እስካሁንም አሉ፡፡

በጅቡቲና በኤርትራ መካከል በራስ ዱሜራ ተራራና ደሴቶች አማካኝት የነበረውን አለመግባባት በሽምግልና ለመፍታት የገባቸው ኳታርና አከራካሪ በሆነው ይዞታ የራስዋን 150 ወታደሮች አስፍራ ቆይታለች፡፡ የኤርትራም ሆነ የጅቡቲ ሠራዊት በስፍራው አልነበሩም፡፡

የገልፉ ሀገራት ኳታርና ለአይሲስ ትረዳለች በሚል ያላቸውን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ እንድታቋርጥ ሲያደርጉና ስድስት የአረብ ሀገራት ይሄንኑ እርምጃ ደግፈው ከሳኡዲ አረቢያ ጎን ሲቆሙ የዲፕሎማቲክ፣ የንግድ ልውውጥና የበረራ ግንኙነት ሲሰርዙ ይህንን ተከትሎ ኳታርና በድንገት በጅቡቲ በሰላም አስከባሪነት አሰማርታቸው የነበሩትን 150 ወታደሮችዋን አስወጥታ ወደ ሀገርዋ ስትወስድ ነው ሻእቢያ አወዛጋቢውን ቦታ በኃይል ገብቶ የያዘው፡፡ በአከራካሪው የራስ ዱሜራ ተራራና ደሴቶች ላይ ሰፈረ፡፡ ወታደሮችም እስከ ግጭት ደረሱ፡፡

ጅቡቲ አቤቱታዋን ለመንግስታቱ ድርጅትና ለአፍረካ ሕብረት አሰማች፡፡ ኢጋድ አጣሪ ኮሚቴ ሰየመ፡፡ የመንግስታቱ ድርጅት ችግሩ በሰለም እንዲፈታ ጥሪ አቅርቦአል፡፡ የራሱን አጣሪ ኮሚቴም ሰይሞአል፡፡ ከአፍሪካ ሕብረትም ጋር እየሰራ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያም ሁለቱ ጎረቤት ሀገራት ጉዳዩን በሰላምና በውይይት እንዲፈቱት ጥሪ አቅርባለች፡፡

ለግዜው ቀጣዩን ለመገመት ባይቻልም ጅቡቲ ከኢትዮጵያ ጋር የጦር ቃል ኪዳን ስምምነት ያላት ሀገር መሆንዋ ይታወቃል፡፡ አካባቢው አስጊ የአለም አቀፍ አሸባሪዎች እንቅስቃሴ የሚካሄድበት፣ የቀይ ባሕር ቀጠና ራሱን ችሎ አለም አቀፍ የባሕር ንግድ

መተላለፊያ ቁልፍ መስመር መሆኑ፣ በሶማሊያ አሁንም ገና ያልተረጋጋ ሰላም መኖሩና የአልሻባብ ሰፊ እንቅስቃሴ ማየል፣ በጅቡቲ የተለያዩ ግዙፍ አለምአቀፍ መንግስታት በጦር ቤዝነት መቀጫ ያደረጉዋት ሀገር መሆንዋ ሲታይ (ፈረንሳይ፣ አሜሪካ፣ ቻይና እና ሌሎችም) ኢትዮጵያን ለጉዳዩ የተለየ ትኩረት እንድትሰጠው ያደርጋታል፡፡

እንዲያውም የኳታር ወታደሮች በሰላም አስከባሪነት ለቀውት የወጡትን የራስ ዱሜራ ተራራና ደሴቶ እኔ ተክቼ ልያዝ ስትል ግብጽ ጠይቃ እንደነበረ የሚገልጡ መረጃዎችም አሉ፡፡ ይሂ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይሆንም፡፡ ለሁሉም ነገ ሌላ ቀን ነውና ቀድሞ እንደ ሀገርና እንደ ሕዝብ ከራሳችን ብሔራዊ ጥቅምና ደሕንነት አንጻር ከውዝግቡ ጀርባም ሆነ ፊት ባሉት ጉዳዮች ላይ ደጋግሞ ማሰብና እርምጃችንን ማስተካከሉ ይበጀናል፡፡